| |
|---|
| 7ኛ ዓመት ቁጥር 5<br>7th Year No. 5 |

| |
|---|
| ሐረር ጥር 23 1994<br>Harar January 31/2002 |

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

# ሐረር ነጋሪ ጋዜጣ

# HARAR NEGARI GAZETA

HARARI PEOPLE NATIONAL REGIONAL STATE

| | | |
|---|---|---|
| የአንዱ ዋጋ 0.50 ብር | በሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ተጠባባቂነት የወጣ | የፖስታ ሣጥን ቁጥር 272 |



ማውጫ

አዋጅ ቁጥር 30/1994

ለሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የ1994 የበጀት ዓመት የመንግስት ሥራዎች ማስፈፀሚያ የታወጀ የተጨማሪ በጀት አዋጅ ቁጥር 30/1994 ዓ.ም ........................ ገፅ 270


## አዋጅ ቁጥር 30/1994

## ለሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የ1994 የበጀት ዓመት የመንግስት ሥራዎች ማስፈፀሚያ የታወጀ የተጨማሪ በጀት አዋጅ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀፅ 52 ንኡስ አንቀፅ 2/ሠ/ መሠረት ክልሉ የራሱን በጀት የማፅደቅና ሥራ ላይ የማዋል ሥልጣን የተሰጠው በመሆኑ፤

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት በክልሉ ህገ መንግስት አንቀፅ 26 ንኡስ አንቀፅ 2/ሀ/ እና በክልሉ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 9/1991 አንቀፅ 21 መሠረት የሚከተለውን የተጨማሪ የበጀት አዋጅ አውጅቷል።

1· **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "በ1994 የበጀት ዓመት ለመንግስት ሥራዎች ማስፈፀሚያ የታወጀ የተጨማሪ በጀት አዋጅ ቁጥር 30/1994" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. ስለተጨማሪ ገቢና ምንጩ

ከፌዴራሉ የመንግስት ግምጃ ቤት እንዲሁም ከተለያዩ የእርዳታና የብድር ምንጮች ከተገኘዉ፤

ከፌዴራል መንግስት የተገኘዉ ተጨማሪ

| | |
|---|---|
| የበጀት ድጎማ | ብር 3,087,800.00 |
| ከዉጭ ብድር | ብር 3,757,900.00 |
| ከክልሉ ህዝባዊና መንግስታዊ ድርጅቶች ብድር | ብር 8,197,000.00 |
| ከክልሉ ግምጃ ቤት | ብር 3,838,800.00 |
| ጠቅላላ ድምር | ብር 18,881,500.00 |

/አሥራ ስምንት ሚሊዮን ስምንት መቶ ሰማኒያ አንድ ሺ አምስት መቶ ብር/ በዚህ አዋጅ መሠረት የሐረሪ ህዝብ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የ1994 ዓ.ም ተጨማሪ በጀት ሆኖ እንዲሰራበት ፀድቋል::

3. ስለ ወጭ ምደባ

ለካፒታል ወጭ

ከዚህ አዋጅ አንቀፅ 2 ላይ የተመለከተዉ ተጨማሪ በጀት በሚከተሉት ዘርፎች ተደልድሎ የወጭ አመደዳቡ ከዚህ በታች በተገለፀዉ ዓይነት ይሆናል::

| | |
|---|---|
| ሀ/ ለድሬጃራ ዉኃ ፕሮጀክት | ብር 15,123,000.00 |
| ለ/ በትምህርትና ጤና ሴክተር | ብር 3,757,900.00 |
| ጠቅላላ ድምር | ብር 18,881,500.00 |

/አሥራ ስምንት ሚሊዮን ስምንት መቶ ሰማኒያ አንድ ሺ አምስት መቶ ብር/ ወጪ ሆኖ እንዲከፈል በዚህ አዋጅ ተፈቅዷል::

4. ክፍያን ስለመፈፀም

ጉዳዩ የሚመለከታቸዉ የክልሉ መንግስት አባላትና መስሪያ ቤቶች ክፍያ ሲጠይቁ የክልሉ ፋይናንስ ቢሮ ከተጠቀሰዉ ምንጭ እንዲከፈል ታዟል::

5. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከጥር 23 ቀን 1994 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል::

ሐረር ጥር 23/1994

ፉአድ ኢብራሂም

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

ፕሬዝዳንት